በ1954ዓ.ም የወጣዉን የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ-ሥርዐት ለማሻሻል ረቂቅ የወንጀል ሕግ ሥነ-ሥርዐት እና የማስረጃ ሕግ ያካተታቸዉ ነጥቦች

ጸሐፊዉ አንተናኔ ጥሩ[1]

መቅድም

የዚህ ጽሑፉ አላማ በ1954 ዓ.ም የወጣዉን እና እስከ አሁን በስራ ላይ ያለዉ የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ[2]ለማሻሻል ረቂቅ የወንጀል ሕግ ሥነ-ሥርዐት እና የማስረጃ[3] የተዘጋጀ ሲሆን ከነባሩ ህግ በተሻለ የተብራራ እና አዲስ ሐሳብ ይዞ በመምጣቱ ምን ምን አካቷል የሚለዉን ለማየት ነዉ፡፡ ጽሑፉን ለመጻፍ ያነሳሳኝ የሕግ አርቃቂወ በሰጡት ስልጠና ተሳታፊ ስለነበርኩ የሕግ አርቃቂዉ የሐሳብ ክፍል ምን እንደነበረ ለሕግ ባለሙያዉ እና ለምስራቅ ጎጃም ከፍተኛ ፍ/ቤት መጽሔት ሕግ አምድ አምባቢያን ግንዛቤ ለመስጠት ካለኝ ፍላጎት ነዉ፡፡ይህ ረቂቅ ሕግ በመሆኑ በፌደራል የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ዉይይት እየተደረገበት እና ቋሚ ኮሚቴ ጉዳዩን እንዲያየዉ የተመራ መሆኑ ይታወቃል ስለሆነም ሕጉ እስካልጸደቀ ድረስ ለሕጉ መዳበር አንዱ ግብዓት ይሆናል፡፡እንዲሁም ይህ ጽሑፍ ለሌሎች ተመራማርያን መነሻ ሐሳብ ይሆናል በሚል እምነት ነዉ፡፡በዚህ ጽሑፉ ለማካተት የተሞከረዉ በ1954ዓ.ም በወጣዉ ወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ ህግ ተገልጸዉ የነበሩት በዚህ አዲስ ረቂቅ ሕግ ተብራርተዉ የወጡትን ሕጎች፣ከኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ (ህገ መንግስቱ[4]፣የወንጀል ህግ[5] እና የወንጀል ፖሊሲ[6]) የተቀዱ መሰረታዉ መርሆች፣ከሌሎች አዋጆች በስራ ላይ ካሉትና በዚህ ረቂቅ ህግ ይሻራሉ ተብለዉ ከሚጠበቁት ሕጎች ተቀድተዉ እና ተሻሽለዉ የወጡትን ህጎች እና በመጨረሻም በረቂቁ የገቡትን አዲስ ጽንሰ ሃሳቦችን ይመለከታል፡፡[7]

መግቢያ

ሕጎች በአጠቃላይ ከይዘታቸዉ አንጻር ዋና(መሠረታዊ) ህጎች እና ቅጽል ሕጎች ተብለዉ በሁለት ይከፈላሉ፡፡ዋና ሕጎች መብት እና ግዴታ በተመለከተ የሚደነግግ የሕግ ክፍል ሲሆን ቅፅል ሕጎች የሥነሥርዓት እና የማስረጃ ሕጎችን የሚያካትት ክፍል ነዉ፡፡ኢትዮጵያ በአብዛኛዉ

---

[1]አንተናኔ ጥሩ(በሕግ ዲግሪ እና ሁለተኛ ዲግሪ ያለዉ የከፍተኛ ፍ/ቤት ዳኛ ሲሆን በዳኝነት ለ15 ዓመት በላይ የሰራ ልምድ ያለዉ ነዉ)፡፡

[2] ከዚህ በኋላ በዚህ በጽሑፉ የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ እየተባለ የሚጠቀሰዉ፡፡

[3] ከዚህ በኋላ በዚህ በጽሑፉ ረ/የወ/ሕ/ሥሥ/ እና ማ/ሕ/ እየተባለ የሚጠቀሰዉ፡፡

[4] ከዚህ በኋላ በዚህ በጽሑፉ የኢ/ፌ/ዲ/ሪ/ሕ እየተባለ የሚጠቀሰዉ፡፡

[5] የኢ.ፌ.ዲ.ሪ.የወንጀል ሕግ አዋጅ፣1996,ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ፣አዋጅ ቁጥር 414፣[ከዚህ በኋላ የወንጀል ህግ ተብሎ በጽሑፉ የሚጠቀስ]፡፡

[6]ኢ/ፌ/ደ/ሪ የወንጀል ፍትህ ፖሊሲ፣የሚኒስተሮች ምክር ቤት፣የካቲት 25፣2003(ከዚህ በኋላ የወንጀል ፖሊሲ ተብሎ የሚጠቀስ)፡፡

[7]ለጽሑፉ አስተዋጸ ያደረጉትን አካላት በሙሉ ምስጋና ይገባቸዋል፡፡ እነሱም የምስራቅ ጎጃም ከፍተኛ ፍ/ቤት የማኔጅመንት አባላት በከፍተኛ ፍ/ቤት መጽሔት የሕግ አምድ ክፍል የሕግ ጽሑፍ እንዳቀርብ በማመቻቸታቸዉ፣የፌደራል ፍትሕ ማሰልጠኛ እና ምርምር ተቋም ከፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ጋር በመተባበር ረ/የወ/ሕ/ሥ/ሥ/ እና ማ/ሕግ በተመለከተ በተሰጠዉ ስልጠና ተሳታፊ እንድሆን በማድረጋቸዉ፣አሰልጣኙም ዶ/ር ስሜነህ ኪሮስ የአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ የሕግ መምህር እና ጠበቃ ሲሆኑ የሕጉ አንዱ አርቃቂ ሲሆኑ ተገቢዉን ስልጠና ሰጥተዉኛል ስለዚህ አክብሮቴ ባሉበት ይድረሳቸዉ፣ፅሑፉን በመገምገም ተገቢ አስተያየት ለሰጠኝ ለአቶ ከፍያለዉ ጌቴ፣አቶ ጌታቸዉ ምህርት እና ለአቶ መኳንንት እጅጉ ምስጋና ይገባችል፡፡ በጽሑፉ ላይ የሚከሰቱት ስህተት እና ግደፈት ጸሐፊዉን ብቻ ይመለከታል፡፡

የኮንቲኔንታል ሕግ ብትከተልም በከፊል የኮመን ሎዉ ማስረጃ ሕግ ለብቻዉ የሚያዘጋጁትን ሐገራትን ትከተላለች።ከዚህ አንጻር በአገራችን የማስረጃ ሕግ በተለያዩ ሕጎች ላይ ተካቶ እና ተሰባጥሮ ስለምናገኘዉ በረ/የወ/ሕ/ሥሥ/ እና ማ/ሕጉ ወጥ በሆነ መልኩ ወንጀልን በተመለከተ የማስረጃ ሕግን ከሥነሥርዓቱ ጋር አካታ በአንድነት ለማቅረብ ሞክራለች።ረቂቅ መግቢያ የወ/መ/ስ/ሕ እና የማስረጃ ሕግ ለማዘጋጀት ያስፈለገዉ ለምንድን ነዉ?ይህ ረቂቅ ሊሸር የፈለጋቸዉ ሕጎች ምን ምን ናቸዉ?፣የረቂቁ መሸጋገርያ ድንጋጌ እና የትርጓሜ ክፍል ምን ምን ያካትታል የሚለዉን ለማየት ጥረት ይደረጋል።

1. በ1954ዓ.ም የወጣዉን የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ሕ ለማሻሻል ረ/የወ/ሕ/ሥሥ/ እና ማ/ሕ/ ማዘጋጀት ያስፈለገዉ ከኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት እና ኢትዮጵያ ከተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ጋር የተጣጣመና መርሆቻቸውንና እሴቶቻቸውን ለማስፈጸም የሚያስችል እንዲሆን ነዉ።ወንጀል ከዘመኑ እድገት አንጻር እየተራቀቀ በመሄዱ በቴክኖሎጂ እድገት አለም ወደ አንድ መንደር(ግሎባላይዜየሽን አስተሳሰብ)እየመጣ በመሆኑ ወቅቱን የዋጀ ዘመናዊ የወንጀል ፍትህ ሂደት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ነዉ።የወንጀል ክርክር የሚመራበትን የሥነ-ሥርዐትና የማስረጃ ድንጋጌ ወጥና አካታች በሆነ መልኩ እንደገና ማደራጀት በማስፈለጉ ነዉ።
2. የረ/የወ/ሕ/ሥሥ/ እና ማ/ሕ/ ሊሸራቸዉ የፈለጋቸዉ ሕጎች የአሁኑ የወ/ሕ/ሥ/ሥ ከወጣ በኋላ የፀደቁትን አዋጆች የወንጀል ምርመራ፣የዳኝነት ስልጣን፣የሥነ-ሥርዐት፣የማስረጃ እና ዓለምአቀፍ ትብብርን ጋር የተያያዙ ድንጋጌዎች በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት የማይኖራቸዉን ዘርዝሮ አቅርቧል።[8]
3. የረቂቁን ሕግ መሸጋገሪያ ድንጋጌ ስንመለከተዉ ይህ ሕግ ከመጽናቱ በፊት የተጀመረ ጉዳይ በተጀመረበት የሥነሥርዓት ሕግ መሠረት ይጠናቀቃል።ይህ ቢኖርም ይህ ሕግ ከመጽናቱ በፊት የተፈጸመ የወንጀል ጉዳይ ተጠርጣሪዉን የሚጠቅም ከሆነ በዚህ ሕግ መሠረት ይመራል።እንዲሁም ይህ ሕግ ከመጽናቱ በፊት ምርመራው ያልተጀመረ የወንጀል ጉዳይ በዚህ ሕግ መሠረት ይመራል።
4. በ1954ዓ.ም የወጣዉ የወ/ሕ/ሥሥ/ሕ ብይን፣ዉሳኔ፣ፍርድ እና ትዕዛዝ ምን ማለት እንደሆነ ባለመተርጎማቸዉ በቃላቶች ትርጉም ላይ ዳኞች ይከራከሩ ነበር።እነዚህን ቃላቶች የምናዉቃቸዉ መስለዉ በስራ ላይ ግን የምንለያይባቸዉ ሲሆን እነዚህን ቃላቶች የምንጠቀምባቸዉ መቸ እና የት ላይ ነዉ የሚሉትን መለየት ተገቢ

[8]የአሁኑ የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ መሻሩ የተጠበቀ ሁኖ በረ/የወ/ሕ/ሥሥ/ሕ ተሽረዉ በአንድ ተጠቃለዉ ይወጣሉ ተብለዉ የታሰቡት ህጎች፦በ(ሀ) የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/1988፤
(ለ)የፀረ ሽብርተኝነት አዋጅ ቁጥር 652/200፤
(ሐ)በሕገ ወጥ መንገድ የተገኘን ገንዘብ ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብ እና ሽብረተኝነትን በገንዘብ መርዳትን ለመከላከል የወጣ አዋጅ ቁጥር 780/2005፤
(መ)የንግድ ውድድርና የሸማቾች አዋጅ ቁጥር 813/2006፤
(ሠ)የፀረ-ሙስና ልዩሥነ - ሥርዐትና የማስረጃ ሕግ አዋጅ 434/2005፤የተሻሻለው የፀረ ሙስና ልዩ የሥነ ሥርዓትና የማስረጃ ሕግ አዋጅ 882/2007፤
(ረ)ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር እና ስደተኞችን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር ወንጀልን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ 909/2007፤
(ሰ)የኮምፒውተር ወንጀል አዋጅ ቁጥር 958/2008፤
(ሸ)የቴሌኮም ማጭበርበር ወንጀል አዋጅ ቁጥር 761/2004 ናቸዉ። ነገርግን ከላይ የተደነገጉት ቢኖሩም ስለ ወታደራዊ ወንጀሎች የተደነገጉ ልዩ የሥነ-ሥርዓት እና ማስረጃ ደንቦች የተጠበቁ ናቸው በማለት በአንቀጽ 2 ተደንግገዉ እናገኘዋቸዋለን።

ነዉ።ለምሳሌ የዋስትና ጉዳይ በተመለከተ መዝገቦችን ስንመለከት አንዳንዱ ዳኛ በዉሳኔ ሌላዉ በብይን እና በትዕዛዝ ብሎ ይሰራል ከዚህ አንጻር የመዝገብ አፈጻጸም ለመያዝ ራሱ አስቸጋሪ ሁኖ የቆየ በመሆኑ መተርጎሙ አስፈላጊ ሁኖ ተገኝቷል።[9]

5. የዚህ ረቂቅ ሕግ ዓላማ መገለጹ የፍትህ አካላት የወንጀል ጉዳዩችን ከምርመራ እስከ ፍርድ ባለዉ ሂደት እና የፍርድ አፈጻጸሙ ድረስ ለመስራት ግልጽ እንዲሆን ታስቦ የተዘጋጀ ነዉ። የየሕጉም አላማ ከታወቀ ሕጉን ለመተርጎም ሆነ ክፍተቱን ለመሙላት ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል።[10]

ከዚህ በመቀጠል በዚህ ጽሁፉ የተካተቱትን ጉዳዮችን ስንመለከት በ1954ዓ.ም የወጣዉ ወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ ሕግ ወጥተዉ የነበሩት በዚህ ረቂቅ ሕግ ተብራርተዉ የወጡትን ህጎች፣(ከአለማቀፍ የሰብዓዊ መብቶች፣ኢትዮጵያ ከተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች፣ከኢ.ፊ.ደ.ሪ ህገ መንግስቱ፣ የወንጀል ህግ ና ወንጀል ፖ/ሲ/ዉ) የተቀዱ መሰረታዉ መርሆች፣ከሌሎች አዋጆች በስራ ላይ ካሉትና በዚህ ረቂቅ ህግ ይሻራሉ ተብለዉ ከሚጠበቁት ህጎች ተቀድተዉ ተብራርተዉ እና ተሻሽለዉ የወጡትን ህጎች እና በመጨረሻም በረቂቁ የገቡትን አዲስ ፅንሰ ሃሳቦችን እናያለን።

ክፍል 1

በ1954ዓ.ም የወጣዉ ወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ ሕግ የነበሩት እና ረ/የወ/ሕ/ሥሥ/ እና ማ/ሕ/ ተብራርተዉ የወጡትን ሕጎች

በ1954 ዓ.ም የወጣዉ ወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ ሕግ ወጥተዉ የነበሩት በዚህ ረቂቅ ሕግ ተብራርተዉ እና ተስፋፍተዉ የወጡትን ሕጎች በተመለከተ ሂደቱን በአጭሩ ለመግለጽ ለፖ/ስ ወይም ለዓ/ሕግ አቤቱታ ወይም ጥቆማ ከደረሰዉ በኋላ ፖ/ሊስ በተጠርጣሪዉ[11] ላይ የወንጀል ምርመራ እንዴት ያካሄዳል?።[12]በምርመራ ወቅት ተጠርጣሪዉ እንዲቀርብ ከተፈለገ ፖ/ሊስ በፅሁፍ መጥርያ ሊያደርሰዉ እና ሊያሳየዉ ይችላል።[13]ነገር ግን ተጠርጣሪዉ ለሕግ ፈቃደኛ ካልሆነ ፖ/ሊስ ተመጣጣኝ ኃይል እንዴት ነዉ መጠቀም የሚችለዉ?[14]፤ቃሉን ተቀብሎ በዋስ የሚወጣ ከሆነ የራስ ዋስትና አቅርቦ እንዲወጣ ይደረጋል።[15]እንዲሁም ተጠርጣሪዉ ከተያዘ በኋላ ፖ/ሊስ ተጠርጣሪዉን ለፍ/ቤት በ48 ሰዓት ዉስጥ በፍ/ቤት በማቅረብ ጊዜ ቀጠሮ ይጠይቅበታል ወይም በዋስትና እንዲወጣ ማመቻቸት ይጠበቅበታል።[16]ፍ/ቤቱም የፖ/ሊስን አቤቱታ በመመርመር

---

[9]በረቂቁ ሕጉ ተተርጉመዋል የምንላቸዉ፦1"ብይን" ማለት በወንጀል ጉዳይ በዋስትና፣በክስ መቃወሚያና የዐቃቤ ሕግ ማስረጃ ከተሰማ በኋላ ተከሳሹ መከላከል እንዳለበትና እንደሌለበት የሚሰጥ ውሳኔ ነው።2 "ውሳኔ" ማለት ከብይን፣ከትዕዛዝና ከፍርድ የተለየ ሆኖ ፍርድ ቤት የሚሰጠው ማንኛውም ውሳኔ ሲሆን የቅጣት ውሳኔን ይጨምራል።3"ፍርድ" ማለት የቀረበን ክስ፣ ክርክር፣ማስረጃ እና ሕግን በመመርመር ተከሳሹ ነፃ ወይም ጥፋተኛ የሚባልበት ነው።4ኛ"ትእዛዝ" ማለት ከውሳኔ የተለየ ሆኖ በፍርድ ቤት የሚሰጥ ማናቸውም ዓይነት የክርክር ማስቀጠያ ወይም ውሳኔ ማስፈፀሚያ ትእዛዝ ነው።

[10]የሕጉ አላማወችን በተመለከተ፦በወንጀል ምርመራ፣ክስ፣ፍርድ ሂደት እና የውሳኔ አፈጻጸም በሕገ መንግሥቱ የተረጋገጡ የሰብዓዊ መብቶችን ማክበር እና ማስከበር፣የወንጀል ፍትሕ እውነትን ማውጣት የሚያስችል፣ ውጤታማ እና ፍትሐዊ እንዲሆን ማድረግ ማስቻል፤እና በወንጀል ፍትሕ ሥርዓቱ ውስጥ የሕግ የበላይነትን ማረጋገጥ ነው።

[11]ለወንድ ፆታ የተገለጸዉ የሴትን ፆታ ያጠቃልላል እንዲሁም ለአንድ ሰዉ የተገለፀዉ ብዙሃንን ያካትታል።

[12]የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት አዋጅ፣1954፣ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ፣አዋጅ ቁጥር 1፣አንቀፅ11-16 (ከዚህ በኋላ በጽሑፉ የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ እየተባለ የሚጠቀሰዉ)።

[13]የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ አንቀጽ 25።

[14]ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 26።

[15]ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 28።

[16]ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 29።

ለተጠርጣሪዉ ዋስትና[17] ወይም ጊዜ ቀጠሮ ይፈቅዳል፡፡[18]በመቀጠልም ፖ/ሊስ ለምስክሮች መጥርያ ያደርስ እና የምስክር ቃል ይቀበላል፡፡ሌላዉ ተጠርጣሪዉ ከመያዙ በፊት ሆነ ከተያዘ በኋላ ፖ/ሊስ ብርበራ ለማካሄድ ከፈለገ የፍርድ ቤት ፈቃድ ያስፈልገዋል ነዉስ አያስፈልገዉም የሚለዉ ነጥብ ከለየ በኋላ የፍ/ቤት ፈቃድ ካስፈለገ ለፍ/ቤት ማመልከቻ ያቀርባል፡፡[19]ፍ/ቤቱም በዝርዝር ብርበራ የሚካሄድበትን ቀን፣ሰዓት፣ቦታ፣የእቃዉ አይነት እና አስፈላጊ ነገሮችን በመግለጽ ለፖ/ሊስ ፈቃዱን ይገልጻል፡፡ፖ/ሊስ ይህን የፍ/ቤት ፈቃድ መሰረት በማድርግ ለተጠርጣሪዉ በማሳየት ብርበራዉን በእማኝ ማህል ካካሄደ በኋላ ለፍ/ቤት ሪፖርት ያደርጋል፡፡እንዲሁም ፖ/ሊስ በብርበራ የተገኙትን ማስረጃወች በኤግዚቢትነት ያስቀምጣል፡፡[20] በተጨማሪም ፖ/ሊስ አስፈላጊ የብርበራ እና የምርመራ ዉጤት እና ማስረጃዎችን ለዓ/ሕግ ያስተላልፋል፡፡[21]ዓ/ሕግም የፖ/ሊስን የምርመራ ዉጤት ካየ በኋላ ያስከስሳል ነዉስ አያስከስስም የሚለዉን በመለየት ክስ የማያስመሰርት ምክንያቶች ሲኖሩ ይኸዉም ማስረጃዉ ያልተሟላ ከሆነ፣በተጠርጣሪዉ ላይ ያልተመሰከረበት ከሆነ፣በህዝብ ጥቅም ጉዳይ የማያስከስስ ከሆነ ዓ/ሕግ መዝገቡን ይዘጋዋል፡፡[22]ክስ የሚያስመሰርትና ከባድ ወንጀል ከሆነ ተጠርጣሪዉ ችሎት እንዲቀረብ ተደርጎ በፌዴራል ደረጃ መጀመሪያ ፍ/ቤት ወይም በክልል ደረጃ ወረዳ ፍ/ቤት ተጠርጣሪዉ ፍ/ቤት እንዲቀርብ ተደርጎ በቀዳሚ ምርመራ ምስክሮች ተሰምተዉ ዉጤቱ ለሚመለከተዉ አካል ይተላለፋል፡፡[23]ስልጣን ያለዉ ዓ/ሕግ ስልጣን ባለዉ ፍ/ቤት መደበኛ ክስ ይመሰርታል፡፡[24]ፍ/ቤቱም ጉዳዩን ያያል፡፡ሌላዉ ቀላል ወንጀል ሲሆን ደግሞ ቀጥታ በግል አቤቱታ የሚቀርብ ከሆነ በግል አቤቱታ አቅራቢነት ክስ ይመሰርት እና ይከራከራሉ፡፡በግል አቤቱታ አቅራቢነት የሚታይ ከሆነ የግል ተባዳይ ያቀረበዉ ክስ በተመለከተ ሆነ በመንግስት የሚታይ ሁኖ ዓ/ሕግ ክስ ከመሰረተ በኋላ ክስ ማንሳት ከፈለጉ ከፍርድ በፊት በማንኛዉ ሰዓት ፍ/ቤቱን መጠየቅ ይችላሉ፡፡ክስ ከተመሰረተ በኋላ ተከሳሽ እንዲቀርብ መጥርያ ወይም የመያዣ ትዕዛዝ ፍ/ቤቱ ይሰጣል፡፡[25]ጉዳዩ በእጅ ከፍንጅ የሚታይ ከሆነ ዓ/ሕግ ክሱን በ72 ሰዓት ዉስጥ

---

[17]በወ/መ/ስ/ስ ህግ 67 መሰረት ዋስትና ለመከልከል ግምት ብቻ በቂ ቢሆንም ነገር ግን ለግምቱ በቂ መንደርደርያ ምክንያት ሊኖር እንደሚገባ ይታመናል፡፡ለምሳሌ ቪዛ በመያዙ ብቻ ተጠርጣሪዉ ከሃገር ይወጣል ተብሎ መደምደም የማቻል መሆኑን በሰበር ተወስኗል፡፡(የፌደራል ጠቅላይ ፍርድቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ዉሳኔዎች፤ቅጽ 7፤መ/ቁ.31734፣የኢፌዲሪ ጠቅላይ ፍርድ ቤት፤አዲስ አበባ፤2000፤ገጽ283-286፡፡(ከዚህ በኋላ የፌ/ጠ/ፍ/ቤ/ሰ/ሰ/ች/ዉ ቅጽ 7 መ/ቁ.31734 ተብሎ በጽሑፉ የሚጠቀስ))፡፡ዋስትና ለመንፈግ በተጠርጣሪዉ ላይ የቀረበዉን የክስ ብዛት እና ከባድነት መነሻ ሊያደረጉ የሚገባ መሆኑን አስገዳጅ ዉሳኔ ተሰጥቷል (የፌ/ጠ/ፍ/ቤ/ሰ/ሰ/ች/ዉ ቅጽ 12 መ/ቁ. 59304)፡፡ተጠርጣሪዉ ዋስትና ከተፈቀደለት በኋላ በወ/ሕ/ሥ/ሥ ቁ.74 መሰረት አዲስ ነገር የተገኘ መሆኑን ዓ/ሕግ ለፍ/ቤት ሲያቀርብ ፍ/ቤቱ አረጋግጦ ዋስትና ሊከለክለዉ የሚችል መሆኑን አስገዳጅ ዉሳኔ ተሰጥቷል(የፌ/ጠ/ፍ/ቤ/ሰ/ሰ/ች/ዉ ቅጽ 12 መ/ቁ.61275)፡፡በዋስትና ዉሳኔዉ ቅሬታ ያለዉ በወ/ስ/ስህ/ቁ.75 መሰረት ይግባኝ ማቅረብ እንደሚቻል አስገዳጅ ዉሳኔ ተሰጥቷል(የፌ/ጠ/ፍ/ቤ/ሰ/ሰ/ች ቅጽ 18 መ/ቁ.110969)፡፡በወቅቱ ይግባኝ ማቅረብ ካልቻለ እና አሳማኝ ምክንያት ካለ ይግባኝ ማስቀጃ ማቅረብ የሚቻል መሆኑን ተወስኖ እናገኘዋልን (የፌ/ጠ/ፍ/ቤ/ሰ/ሰ/ች ቅጽ 7 መ/ቁ.39722)፡፡

[18] የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ አንቀጽ 59፡፡

[19] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 32-33፡፡

[20] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 97፡፡

[21] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 33-34፡፡

[22] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 42፡፡

[23] ተጠርጣሪዉ በቀዳሚ ምርመራ ወቅት ፍ/ቤት ባይቀርብ ምስክሮች ይሰማሉ ነዉስ አይሰሙም የሚለዉ አከራካሪ ነጥብ ስለሆነ ሕጉ ሲጸድቅ በግልጽ ቢቀመጥ መልካም ነዉ እላለሁ፡፡

[24]ዓ/ሕግ ለፍ/ቤት ክስ ሲያቀርብ የተጠርጣሪዉን ድርጊት እና ፍሬ ነገር የወ/ስ/ስ/ህ/ቁ 111 እና 112 መሰረት በማድረግ በግልጽ ነዉ ማቅረብ ያለበት(በፌ/ጠ/ፍ/ቤ/ሰ/ሰ/ች ቅጽ 15 መ/ቁ 91535)፡፡ዓ/ሕግ ክስ ሲመሰርት በወ/ሕ/ሥ/ሥ ቁ.101 ወንጀል እና የካሳ የፍትሐ ብሔር ክስ መመስርት እንደሚችል ተደንግጎ እናገኘዋለን ነገር ግን ብዙ ጊዜ በተግባር አልተለመደም፡፡

[25] የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ አንቀጽ 49-55፡፡

አዘጋጅቶ እና ፖሊስ ተከሳሽን እና የግራቀኝ ምስክሮችን አሟልቶ ለፍ/ቤት እንዲያቀርብ ይደረጋል፡፡ተከሳሹ ጠበቃ የማማከር መብቱ ተጠብቆ[26] ክሱ እና ማስረጃዉ ይሰማል፡፡እጅ ከፍንጅ ሆነ መደበኛ ክስ ሁኖ ጉዳዩ እልባት ካልተሰጠዉ በስተቀር ተከሳሽ ሲቀርብ ዋስትናዉን በተመለከተ በወ/ሥ/ሕ/ሥ ቁጥር 67 መሰረት የሁኔታ ክልከላ ሲኖር ይኸዉም ተከሳሽ በፍ/ቤት ማስረጃ ያጠፋል ተብሎ ካልተጠረጠረ፣እራሱ ተከሳሽ ይጠፋል ተብሎ የሚገመት ካልሆነ በስተቀር ተጠርጣዉ በዋስ ይወጣል፡፡በወ/ሕ/ሥ/ሥ ቁጥር 63 በተደነገገዉ መሠረት በተከሳሽ የወንጀል ድርጊት ምክንያት የሞተ ሰዉ ካለ እና ከ15 ዓመት በላይ የሚያስቀጣ ከሆነ ዋስትና ይከለከላል፡፡ነገር ግን በረቂቁ የሁኔታ ክልከላ ካልኖረ በስተቀር ተጠርጣሪ(ተከሳሽ) በዋስ መዉጣት ይችላል ተብሎ መደንገጉ አላራላሪ ጉዳይ ሁኗል፡፡ዋስትና ህገመንግስታዊ መብት እና ዋስትና መከልከል በጠባቡ የሚተረጎም ቢሆንም በግድያ የተጠረጠረ(የተከሰሰ) ሰዉ ቤተሰቦቹ በበቀል መግደል በሃገራችን ያለ፣እስከአሁን ያልተቀረፈ ባህል መሆኑ በዋስ ሁኖ በዉጭ መከራከሩ ለሌላ ወንጀል በር ከፋች ይሆናል፡፡እንዲሁም በአገራችን የወንጀል ምስክር እና ጠቋሚወች አዋጅ ቢኖርም ለምስክሮች ሆነ ለጠቋሚወች ተገቢዉን ጥበቃ ባለመደረጉ ከዘመድ ዉጭ በዓይ ሰዉ አንመሰክርም በማለታቸዉ ቤተሰብ ተደራጅቶ በመመስከር ተከሳሽን ያስቀጡታል ወይም የሚች ቤተሰብ ያላዩትን አይተናል በማለት በሐሰት ስለሚመሰክሩ ትክክለኛ ተጠርጣሪወች የተያዙ ቢሆንም በማስረጃ ምዘና ተከሳሹ ነጻ ይሆናል፡፡ይህ ሲሆን ፍትህ እንዳይሰፍን ይሆናል፡፡ተጠርጣሪዉ (ተከሳሽ) ሰዉ ገሎ በጉልበት ሆነ በኢኮኖሚ አቅም ያለዉ ከሆነ የግል ተበዳይን ቤተሰብ እንዳትመሰክሩ፣ከመሰከራችሁ እገላችኋለሁ በሚል ተጽኖ የመፍጠር እድሉ ሰፊ ስለሆነ ፍትህን ለማረጋገጥ እንቅፋት ይሆናል፡፡ተከሳሽ ዋስ ተክልክሎ አላግባብ ከታሰረ ካሳ በረቂቁ ህግ የመጠየቅ መብት ያለዉ ስለሆነ እንዲሁም ጉዳዩ በቆየ ቁጥር መረጋጋት ስለሚኖር፣ተጨማሪ ወንጀል እንዳይከሰት የራሱ በጎ አስተፅኦ ስላለዉ ሆን ብሎ ሰዉ ገሏል ተብሎ የተጠረጠረን በዋስ መዉጣቱ አግባብ አይደለም በማለት ይከራከራሉ፡፡ከላይ ከተገለጹት ምክንያቶች አንጻር ዋስትና ሰፊ መብት መሆኑን ቢታመን፣በዚህ ጉዳይ ግን ተጠርጣሪዉ(ተከሳሽ) ዋስ ተክልክሎ ማረሚያ ቤት መቆየቱ የተሻለ ይሆናል፡፡

ለተከሳሽ መጥርያ ተልኮለት ካልቀረበ እና ጉዳዩ በሌለበት የሚታይ ካልሆነ በስተቀር ተከሳሽ ጠበቃ የማማከር መብቱ ተጠብቆ ክስ መሰማት ሲጀምር የተከሳሽ ማንነት ለማወቅ የተከሳሽ ስም፣እድሜ፣ስራ፣የትምህርት ደረጃ፣የቤተሰብ ሁኔታዉን በመጠየቅ ይረጋገጣል፡፡ለወጣት ተጠርጣሪ[27] ያለዉ ሥነሥርዓት የተጠበቀ ሁኖ በመደበኛዉ ክስ ለተከሳሽ ክሱ ተነቦለት የእምነት ክህደት ቃሉን[28] ተጠይቆ ተቃዉሞ ካለዉ ይጠየቃል፡፡ተከሳሽም በተቃዉሞዉ ከዚህ በፊት የተከሰሰ እና ጥፋተኛ ወይም ነጻ ተብሎ የነበረ መሆኑን፣ጉዳዩ በይርጋ የታገደ ከሆነ እና ሌሎች ተቃዉሞ ከቀረቡ ፍ/ቤቱ ተቃዉሞዉን[29]በመመርመር ተቃዉሞዉን ከተቀበለ መዝገቡን

---

[26] ከባድ ወንጀሎች ከሆኑ ተጠርጣሪዉ(ተከሳሽ) ጠበቃ በግሉ መቅጠር ካልቻለ መንግስት የመመደብ ህገመንግስታዊ ግዴታ ያለበት መሆኑን በሕገ መንግስት አንቀጽ 20(5) ተደንግጎ እናገኘዋለን እንዲሁም አስገዳጅ ዉሳኔ ተሰጥቶበታል (በፌ/ጠ/ፍ/ቤ/ሰ/ሰ/ች ቅጽ 13 መ/ቁ.65566)፡፡

[27] ህጻናት እና ወጣት ተጠርጣሪወች በሕገመንግስት አንቀጽ 36(2)፣የአፍሪካ ህጻናት መብቶች ቻርተር አንቀጽ 4(1)፣የወንጀል ሕግ ቁጥር 53 እና 168፣በወ/ሕ/ሥ/ሥ ቁ.172 እና ተከታዮች መሰረት የወጣት ጥፋተኞች በጥንቃቄ ጉዳዩ ሊታዩ እና ፍርድ ሊሰጡ የሚገባ መሆኑን ዉሳኔ ተሰጥቷል (በፌ/ጠ/ፍ/ቤ/ሰ/ሰ/ች ቅጽ 20 መ/ቁ.118130)፡፡

[28]ተከሳሽ የእምነተ ክህደት ቃሉን ሲጠየቅ ካመነ ፍ/ቤቱ በዝርዝር መመዝገብ ያለበት እና በክሱ የተገለጸዉ ፍሬ ነገር በድርጊት መፈጸሙን እና ሕጉን መተላለፉን ተረጋግጦ መወሰን እንዳለበት በወ/ሕ/ሥ/ሥ 134 እና በሰበር ተወስኗል(በፌ/ጠ/ፍ/ቤ/ሰ/ሰ/ች ቅጽ 18 መ/ቁ.111742)፡፡

[29]ተቃዉሞ በወ/ሕ/ሥሥ/ሕ አንቀጽ 130 የተዘረዘርዉ ብቻ አይደለም ሌሎችም ተቃዉሞወች ሊቀርቡ የሚችሉ መሆኑን በኢ/ፌ/ደ/ሪ ሕገመንግስት አንቀጽ 5(2)፣13(1)፣22(1) እና አለም አቀፍ የሲቪል እና የፖለቲካ መብቶች ቃልኪዳን ስምምነት (ICCPR)፣አንቀጽ 15(1) በፌ/ጠ/ፍ/ቤ/ሰ/ሰ/ች ቅጽ 14 መ/ቁ.73514 ተወስኖ እናገኘዋለን፡፡ነገር

ይዘጋዋል፡፡ተቃዉሞዉን ካልተቀበለዉ የዓ/ሕግን ማስረጃ[30] ይሰማል፡፡ፍ/ቤቱም መዝገቡን በመመርመር በተከሳሽ ላይ ካልተመሰከረበት በነጻ ይሰናብታል፡፡ በሌላ በኩል ከተመሰከረበት ይከላከል ተብሎ ብይን ይሰጥና[31]መከላከያ ምስክር ተከሳሽ ካለዉ እንዲያሰማ ይደረጋል፡፡[32]ፍ/ቤቱም ሙሉ መዝገቡን በመመርመር የነጻ ወይም የጥፋተኝነት ፍርድ ይሰጣል፡፡[33]ተከሳሽ ጥፋተኛ ከተባለ ፍ/ቤቱ የግራቀኙን የቅጣት አስተያየት ከተቀበለ በኋላ ተገቢውን የቅጣት ዉሳኔ ይሠጣል፡፡[34]ቅጣቱን በተመለከተ እስራት ከሆነ ተከሳሽ በዋስ እየተከራከረ ከሆነ ፖሊስ ተከሳሽን ለማረሚያ እንዲያስረክብ ይታዘዛል፡፡ሌላዉ ተከሳሽ ዋስትና የተከለከለ እና ማረሚያ ካለ ማረሚያ ቤት እስራቱን እንዲያስፈጽም ፍ/ቤቱ ትዕዛዝ ይጽፍለታል፡፡በፍርዱ ሆነ በቅጣቱ ቅር የተሰኘ ወገን ፍርደኛ ወይም ዓ/ሕጉ ጉዳዩን በይግባኝ መብት አለዉ፡፡የተከሳሽ ወይም የዓ/ህግ የይግባኝ መብቱ ከተጠናቀቀ ደረጃዉን ጠብቆ በክልል ወይም በፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በሰበር[35] እንዲታይላቸዉ መጠየቅ ይችላል፡፡እንዲሁም የተከሰሰበት ወንጀል የሚያስቀጣው በአሁን ወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ ከ12 ዓመት በላይ የሚያሥቀጣ [36]ወይም በረ/ወ/ሕ/ሥ/ሥ/ሕ ድንጋጌ መነሻ ቅጣቱ 7 ዓመት የሆነዉ ፍርደኛ በሌለበት ጉዳዩ ከታየ መጥርያዉ በአግባቡ ያልደረሰዉ መሆኑን[37] የሚያስረዳ ማስረጃ ካለዉ እኔ ባለሁበት ልከራከር ብሎ ለፍ/ቤት ማመልከቻ ማቅረብ ይችላል፡፡

ግን በፍትሐ ብሔር ሐላፊነት የለብህም ስለተባልኩ በወንጀል ተጠያቂ ልሆን አይገባም ብሎ መቃወም የማይቻል መሆኑን (በፌ/ጠ/ፍ/ቤ/ሰ/ሰ/ች ቅጽ 15 መ/ቁ.78470)፡፡

[30]ማስረጃ የመስማት ሆነ የማሰማት ሕገመንግስታዊ መብት ነዉ፡፡እንዲሁም በአለም አቀፍ የሰባዓዊ ድንጋጌወች ተደንግጎ እናገኘዋለን፡፡ፍ/ቤቱ የሰዉ እና የሰነድ ማስረጃ አስፈላጊ ከሆነ ተጨማሪ የባለሙያ ምስክርነት ሊሰማ ይችላል ፡፡ማስረጃወች ቀጥታ ወይም የአካባቢ ማስረጃ ሊሆን ይችላሉ፡፡ከተጠርጣሪወች ለምስክርነት ይሆነኛል ብሎ ዓ/ህግ ሊመርጥ ይችላል፡፡ይህ የወንጀል ማስረጃ ተመሳሳይ ከሆነ ለፍትሃብሐር ማስረጃ ሊሆን ይችላል፡፡ከላይ የተገለጹትን መሰረት በማድረግ ፍ/ቤቱ በክሱ የተገለጸዉ ፍሬ ነገር እና በማስረጃ የተገለጸዉ ድርጊት ሲመዘን ህጋዊ፣ግዙፋዊ፣ሞራላዊ መሰረት ተደርገዉ ነዉ፡፡ስለማስረጃ ህግ የበለጠ ለመረዳት (በፌ/ጠ/ፍ/ቤ/ሰ/ሰ/ች ቅጽ 19 መ/ቁ.111498፣ቅጽ 19 መ/.109441፣ቅጽ 19 መ/ቁ.113464፣ቅጽ 17 መ/ቁ.100712፣ቅጽ 17 መ/ቁ.92141፣ቅጽ 7 መ/ቁ.31731፣ቅጽ 13 መ/ቁ.75922፣ቅጽ 13 መ/ቁ.75980፣ቅጽ 13 መ/ቁ.71184፣ቅጽ 13 መ/ቁ.71184፣ቅጽ 13 መ/ቁ.46386፣ቅጽ 13 መ/ቁ.57988፣ቅጽ 13 መ/ቁ.75980) ዉሳኔ የተሰጠባቸዉ ስላሉ መመልከት ይቻላል፡፡

[31]ተከሳሽ ተከላከል ተብሎ ብይን መሰጠቱ የመጨረሻ ፍርድ ስላልሆነ በይግባኝ ተቀባይነት የማይኖረዉ መሆኑን ተወስኖ እናገኘዋለን (በፌ/ጠ/ፍ/ቤ/ሰ/ሰ/ች ቅጽ 12 መ/ቁ.59537)፡፡

[32]ተከሳሽ መ/ምስክር የማሰማት መብት ያለዉ መሆኑን በሕገመንግስት አንቀጽ 20(4)፣ወ/መሕሥ/ሥ/ቁ.(199(ሀ)፣123፣202(3) እና የሲቪል እና የፖለቲካ መብቶች አለም አቀፎች ቃልኪዳን አንቀጽ 14(3)(ለ) ተደንግጎ እናገኘዋለን፡፡(የሲቪል እና የፖለቲካ መብቶች አለም አቀፎች ቃልኪዳን፣በጠቅላላ ጉባየዉ የተዘጋጀዉ በ2200A (XXI),አንቀፅ 14(3)(ለ)፣atWWW <http://www2.ohchr.org/english/law/ccpr.htm> (consulted 14 August 2008) ነገርግን ተጠርጣሪዉ መ/ምስክር በተደጋጋሚ እድል ተሰጥቶት ካላቀረበ ወይም ክስ ከተሰማ በኋላ ለመከራከር ፈቃደኛ ካልሆነ የመከራከር ሕገመንግስታዊ መብቱ ታልፎ በተጠርጣሪዉ ተገቢዉን ፍርድ የሚሰጥ መሆኑን ተዋሰኗል፡፡(በፌ/ጠ/ፍ/ቤ/ሰ/ሰ/ች 4 መ/ቁ.12025)፡፡

[33]የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ አንቀጽ 142-149፡፡

[34]የተሻሻለዉ የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመርያ፣2006፣መመርያ፣አዋጅ ቁጥር 2፡፡

[35]ሰበር ሰሚ ችሎት ስልጣኑ የሕግ ስህተት ሲኖር ጉዳዩን ማየት ሲሆን ማስረጃ (ፍሬ ነገር) የመመዘን ስልጣን የሌለዉ ቢሆንም የስር ፍ/ቤቶች የማስረጃ መርህን በጣሰ ያስተናገዱ ከሆነ ሰበር ሰሚዉ ችሎት ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለዉም ሊባል የማይቻል መሆኑን ተወስኖ አድሯል፡፡(በፌ/ጠ/ፍ/ቤ/ሰ/ሰ/ች 20 መ/ቁ.113143፣ቅጽ 13 መ/ቁ.63014 እና ቅጽ 17 መ/ቁ.89676)፡፡

[36]የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ አንቀጽ 161 ነዉ፡፡

[37]በሌለበት ዉሳኔ ተሰጥቶ ለተጠርጣሪዉ ቀደም መጥርያ በአግባቡ አለመድረሱ ከተረጋገጠ ባለበት ክርክሩ እንዲቀጥል የሚወሰን መሆኑን እዚህ ላይ ወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ አንቀጽ 199 እና ተከታዮች ተድንግጎ እናገኘዋለን፡፡ እንዲሁም በፌ/ጠ/ፍ/ቤ/ሰ/ሰ/ች ቅጽ 16 መ/ቁ.94227፣ ቅጽ 17 መ/ቁ.93577 ተወስኖ እናገኘዋለን፡፡ተጠርጣሪዉ በሌለበት ይከራከር የሚባለዉ ክስ ከመሰማቱ ጀምሮ መሆኑን ነገር ግን በቅጣት ዉሳኔ በቀረ ሁሉ በሌለበት ሊባል የማይገባዉ መሆኑን ቅጽ 13 መ/ቁ.76909 ተወስኖ እናገኘዋለን፡፡

ሌላዉ ስለመሰየም[38]፣ወጣቶች የሚዳኙበት፣[39]የወንጀል እና የፍትሃብሄር የካሳ ክስ አጣምሮ ማቅረብ እና ደንብ መተላለፍ ስለ ሚመራበት ሥነ ሥርዐት[40] በዝርዝር ተደንግጎ እናገዋለን፡፡

ክፍል 2

ኢትዮጵያ ከተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች፣ከኢ.ፌ.ደ.ሪ (ሕገ መንግስቱ፣ ወንጀል ህግ እና ወንጀል ፖሊሲ) የተቀዱ መሰረታዉ መርሆች

በረቂቁ ወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ እና ማስረጃ ሕግ መሠረታዊ መርሆዎች የተካተተዉ የአለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶችን መነሻ ያደረገዉ በኢ.ፌ.ደ.ሪ ሕገመንስት እና በወንጀል ፖሊሲ መሰረት ያደረገዉ እንዲሁም የሕግ ባለሙያዎች ሕገመንግስት የመተርጎም ስልጣን ስለሌለን እነዚህን መርሆዎችን በስራ ላይ መተርጎም አንችልም በሚል እንዳይተዋቸዉ እና በዚህ ሕግ ተካተዉ መቅረባቸዉ ለስራዉ አመችነት እና ቅለት ይኖርዋል ተብሎ በዚህ ረቂቅ ሕግ ተካተዉ ቀርበዋል፡፡እነሱም፦

- ተጠርጣሪዉ(ተከሳሽ) የጥፋተኝነት ፍርድ እካልተሰጠዉ ነፃ ሆኖ የመገመት መብት አለዉ፤[41]
- በአንድ የወንጀል ድርጊት ድጋሜ ሊከሰስ አይገባዉም፡፡[42]ከተከሰሰም ለፍ/ቤቱ ታቀዉሞ አቅርቦ ድጋሜ መከሰሱ ከተረጋገጠ ተቀባይነት ይኖርዋል፤[43]
- በሕግ ፊት ልዩነት (በጾታ፣በሃይማኖት፣በዘር በመሳሰሉት)ሳይኖር በእኩልነት ይዳኛሉ፡፡[44]
- ሕጋዊ ምክንያት ሳይኖር አላግባብ ማንኛዉንም ግለሰብ መያዝና ማሰር አይቻልም፡፡እንዲሁም ከተያዘ በኋላ ድብደባ የአካል ሆነ የሞራል ጉዳት የሚያደርስ ኢ-ሰብዓዊ አያያዝ ሊኖር አይገባዉም፡፡[45]የተያዘ ተጠርጣሪ ጠበቃ ወክሎ የመከራከር መብት አለዉ ከባድ ወንጀሎች ከሆኑ መንግስት ጠበቃ የማቆም ሐላፊነት አለበት፡፡[46]
- ፍ/ቤቱም የተጠርጣዉን ጉዳይ በተፋጠነ ዉሳኔ መስጠት አለበት፡፡
- ፍ/ቤቱም የፌደራል ሆነ የክልሉን መግባቢያ ቋንቋ መሰረት አድርጎ ተጠርጣሪዉን ማስተናገድ አለበት፡፡ተከሳሽ ቋንቋዉን ካላወቀዉ በተርጓሚ እንዲስተናገድ ይደረጋል፡፡[47]
- ተጠርጣሪዉ የሚቀጣዉ ድርጊቱ በወንጀል ሕግ ወንጀል ነዉ ተብሎ ተደንግጎ ሲገኝ ነዉ፡፡
- በግል አቤቱታ የሚቀርብ ካልሆነ በስተቀር የወንጀል ክስ የመንግሥት ነዉ፡፡

---

[38]ስለመሰየም በወንጀል ህግ ተደንግጎ እናገኘዋለን በመሰየም ሊያገኝ የሚችለዉን መብት ከመሰየሙ አስቀድሞ በቅጣት ቀሪ ሆኖበት የነበረዉን መብት ሳይሆን ወደፊት ሊጠቀምበት የሚገባዉን መብት ብቻ ስለመሆኑ ቅጽ 14 መ/ቁ.61221 ዉሳኔ ማየት ይቻላል፡፡

[39]ረ/የወ/ሕ/ሥሥ/ እና ማ/ሕ/ 376-385፡፡

[40] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 386-393፡፡

[41]የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት፣1987፣ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ፣አዋጅ ቁጥር 1፣1ኛ ዓመት፣ቁጥር 1 አንቀፅ 20(3)((ከዚህ በኋላ በጽሁፉ ህገመንግስት እየተባለ የሚጠቀሰዉ)፡፡

[42]በተመሳሳይ ድርጊት ድጋሚ ክስ ሊቀርብ አይገባም እንዲሁም ተጠርጣሪዉ በአካል ጉዳት ማድረስ ወንጀል ተከሶ የግል ተበዳይ ቢሞት ድጋሜ በግድያ ሊከሰስ የማይገባዉ መሆኑን በሕገመንግስት 23 እና በዝርዝር (በፌ/ጠ/ፍ/ቤ/ሰ/ሰ/ች ቅጽ 13 መ/ቁ.65325፣ ቅጽ 15 መ/ቁ.85237፣ቅጽ 13 መ/ቁ.14 መ/ቁ.72304 ፣ ቅጽ 13 መ/ቁ.72304)ተወስነዉ ስለምናገኝ ዝርዝሩን መመልከት ይቻላል፡፡

[43] የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ አንቀጽ 130 ነዉ፡፡

[44] ሕገመንግስት አንቀጽ 25 ነዉ፡፡

[45]ሕገመንግስት አንቀጽ 18(1)::

[46] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 20(5)::

[47] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 19(1) እና 20(7)፡፡

- የፍትህ ተቋማት አላማቸዉ እውነትን ማውጣት እና አጥፊዉ ተለይቶ ለእሱ ሆነ ለመሰሎቹ አስተማሪ ቅጣት እንዲያገኝ ነው በሚል ተደንግገዉ እናገኛቸዋለን፡፡[48]

ክፍል 3
ከሌሎች አዋጆች በስራ ላይ ካሉትና በዚህ ረቂቅ ህግ ይሻራሉ ተብለዉ ከሚጠበቁት ህጎች ተቀድተዉ ተብራርተዉ እና ተሻሽለዉ የወጡትን ህጎች

በዚህ ክፍል የምናያቸዉን እንደሚከተለዉ ለመግለጽ ጥረት ተደረጓል አነሱም፦

1. በወንጀል ፖሊሲዉ ሆነ በተቋማት ማቋቋሚያ አዋጆች የተገለጹት ነጥቦች ተካተዉ የምናገኛቸዉ ‹‹የፍትሕ ተቋም››የምንላቸዉ የፌዴራል ወይም የክልል ፖሊስ፣ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ፣ፍርድ ቤት፣ ማረሚያ ቤትና የተከላካይ ጠበቃ ተቋምን ያጠቃልላል፡፡የፍት ተቋም የወልና የጋራ ተግባርና ኃላፊነት በተመለከተ የወንጀል ፍትሕ ሥርዓቱ ሚዛናዊነት፣ቀልጣፋነት፣ተገማችነት እና ግልጽነት በማረጋገጥ ውጤታማ እና ወጭ ቆጣቢ እንዲሆን ያደርጋሉ፤የሕዝብ ተዓማኒነትና ፍትሐዊነትን የሚያረጋግጥ ሥርዓት ይዘረጋሉ፤በወንጀል ጉዳይ ጥናትና ምርምር ያደርጋሉ፤ዘመናዊ አሰራርንም ይዘረጋሉ፤የወንጀልመረጃእናስታቲክስንያሰባስባሉ፣ያደራጃሉ፣ይተነትናሉ፣ያሰራጫሉ፣የቅሬ ታ እና የአቤቱታ አቀራረብ ሥርዐትን ይዘረጋሉ፤የተጠርጣሪ፣ተከሳሽ፣ተጎጂ፣ምስክር እና ታራሚ አያያዝ ሥርዐት የሕገመንግሥቱን እና የዚህን ሕግ ድንጋጌዎች በጋራ የሚያሰራቸዉን የተከተለ መሆኑን ያረጋግጣሉ፤ሌሎችን በጋራ የሚያሠሩ ስራወችን ተግባራዊ ያደርጋሉ፡፡እንዲሁም የእያንዳንዳቸዉን የፍትህ ተቋማት ተግባር እና ሃላፊነት ስናይ፦
    - ፖሊስ ምርመራ ያካሄዳል፤ ከምርምራ ጋር በተያያዘ ማስረጃ ያሰባስባል፤ብርበራ በተጠርማሪዉ አካል እና ንብረት ያካሄዳል፣በብርበራ የተገኘዉን ንብረት በኤግዚቪትነት ይይዛል፤መጥሪያ ለተከሳሽ እና ለምስክር ያደርሳል፤ተጠርሪዉን (ከሕግ አማካሪው፣ከሐኪሙ ወይም ከኃይማኖት አባቱ)ለማገናኘት እንዲሁም ከጓደኛው ወይም ከቅርብ ዘመዶቹ ጋር በግል የሚገናኝበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤በምርመራ ወቅት በማቆያ ቤት የሚቆዩ ተጠርጣሪዎች አያያዝ ሰብዓዊ ክብራቸውን እና መብታቸውን የጠበቀ እንዲሆን የሚያስችል በሆነ መልኩ ያደራጃል፡፡[49]
    - የዐቃቢ ሕግ ተቋም ተግባርና ኃላፊነት የወንጀል ምርመራን በበላይነት ይመራል፤በምርመራ መዝገብ ላይ ውሳኔ ይሰጣል፤በፍርድ ቤት ክርክር ያደርጋል፤ክስ ያነሳል[50]፤ከክስ በፊት በኤግዚቢት[51] ላይ ውሳኔ ይሰጣል፤ለተከሳሽ በመከላከያ ማስረጃነት ሊጠቅም የሚችል ማስረጃን ለተከሳሽ ይሰጣል፣የፍርድ

[48]የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ሕግ ሥነ-ሥርዓት እና የማስረጃ ሕግ ,ረቂቅ,አንቀጽ 4-17(ከዚህ በኋላ ረ/የወ/ሕ/ሥ/ሥ/ እና ማ/ሕ/ ተብሎ በዚህ ጽሁፍ ይገለጻል)፡፡

[49] የፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን መተዳደርያ ደንብ፣2005፣ነጋሪት ጋዜጣ ፣ደንብ ቁጥር 268፡፡

[50]ዓ/ሕግ በወ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ.122(1) መሰረት ክስ ማንሳት ይችላል ክስ ካነሳ በኋላ እንደገና መዝገቡ እንዲንቀሳቀስለት መጠየቅ ይችላል ነገርግን በአዲስ መዝገብ ይህን ጉዳይ ይዞ ክስ መመስረት የማይችል መሆኑን አስገዳጅ ዉሳኔ ተሰጥቶታል፡፡(በፌ/ጠ/ፍ/ቤ/ሰ/ሰ/ች ቅጽ 21 መ/ቁ.127312)፡፡

[51]በፖሊስ ያለ ኤግዚቪት ላይ ዓ/ሕግ የሚበለሽ ንብረት ከሆነ ተሸጦ ገንዘቡ በአደራ እንዲቀመጥ ያመቻቻል፣ክርክር ተካሂዶበት ውሳኔ ሲሰጥ ፍ/ቤቱ እርግጠኛ ከሆነ በወንጀል መዝገቡ ዉሳኔ ይሰጣል፡፡ፍ/ቤቱ እርግጠኛ ካልሆነ የፍትሐብሄር ክርክር በሌላ መዝገብ ተካሂዶ ውሳኔ ይሰጣል፡፡ስለኤግዚቪት በዝርዝር (በፌ/ጠ/ፍ/ቤ/ሰ/ሰ/ች ቅጽ 21 መ/ቁ.126017 እና ቅጽ 3 መ/ቁ.10797) መመልከት ይቻላል፡፡

ቤት ዉሳኔዎችና ትዕዛዞች መፈጸማቸውንና መከበራቸውን ይከታተላል፤ማረሚያ ቤትን ይጎበኛል፤የይቅርታ አሰጣጥ አፈጻጸምና ክትትል ሥርዐትን[52] ከሚመለከታቸው ሌሎች አካላት ጋር በመተባበር ይዘረጋል።[53]

- የፍርድ ቤት ተግባርና ኃላፊነት በተመለከተ ፍ/ቤት የጊዜ ቀጠሮ፤የብርበራ፤የመያዣ እና ሌሎች ቅድመ ክስ ተግባራትን በተመለከተ አስፈላጊውን ትእዛዝ ይሰጣል፤ ፍርድ ቤት የቀረበ ተከሳሽ እና ምስክር የፍርድ ቤቱን የሥራ ቋንቋ የማይረዳው ወይም በምልክት ቋንቋ መግለጽ አስፈላጊ እንደሆነ አስተርጓሚ ይመድባል፤የቀረበ የወንጀል ክስን ይመረምራል፤ያከራክራል፤እንደ አግባብነቱ ትእዛዝ፤ብይን፤ፍርድ ወይም ውሳኔ ይሰጣል፤የሰጠውን ውሳኔ ያስፈጽማል ወይም እንዲፈጸም ያደርጋልበ፤በሕመም ምክንያት ችሎት መቅረብ የማይችል ሰው ወይም ለጥቃት የሚጋለጥ ምስክር ችሎት ሳይቀርብ የምስክርነት ቃሉን የሚሰጥበት ሁኔታ ያመቻቻል፤ በንብረት ላይ የእግድ ትእዛዝ ይሰጣል፤እንደ አስፈላጊነቱ የታገደ ንብረትን የሚያስተዳድር አካል ይሾማል ወይም ንብረቱ እንዲወረስ ትእዛዝይ ይሰጣል።[54]
- የማረሚያ ቤት ተግባር እና ኃላፊነት በፍርድ ቤት ትእዛዝ በጥበቃ ሥር ያለ ተከሳሽ የወንጀል ምርመራ ወይም ክርክር እስከ ሚጠናቀቅ ድረስ በማረፊያ ቤት ያቆያል፤ጥፋተኛ የተባለን ያርማል፤ታራሚዎች ከሕብረተሰቡ ጋር መልሶ እንዲቀላቀሉ ያደርጋል፤ታራሚ ወይም ተከሳሽ ከሕግ አማካሪው፤ከጓደኛው፤ከሐኪሙ ወይም ከኃይማኖት አባቱ እንዲገናኝ ያመቻቻል እንዲሁም ከጓደኛው ወይም ከቅርብ ዘመዶቹ ጋር የሚገናኝበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤በማረፊያ ቤት የሚገኝ ተከሳሽን እና በማረሚያ ቤት ያለ ታራሚን ለፍርድ ቤት ያቀርባል፤በማረፊያ ወይም ማረሚያ ቤት የሚቆዩ ሰዎች በዕድሜ፤በጾታ፤ሕግ በሚፈቅደው አግባብ በወንጀል ዓይነት፤በቅጣት እና በጤና ሁኔታ ተለያይተው እንዲያዙ ያደርጋል፤በማረፊያ ወይም ማረሚያ ቤት የሚቆዩ ሰዎችን አያያዝ ሰብዓዊ መብታቸውን እና ክብራቸውን የጠበቀ እንዲሆን ያደርጋል፤የአመክሮ አሰጣጥ አፈጻጸም እና ክትትል ሥርዐትን ከሚመለከታቸው ሌሎች አካላት ጋር በመተባበር ይዘረጋል፤ተግባራዊነቱን ይከታተላል።[55]
- የተከላካይ ጠበቃ ተቋም ተግባርና ኃላፊነት ተጠርጣሪው ወይም ተከሳሹ ወይም ታራሚው በተጠረጠረበት ወይም በተከሰሰበት ወይም በተፈረደበት የወንጀል ጉዳይ የጥብቅና አገልግሎት ይሰጣል፤ጉዳዩ ያለበትን ደረጃም ለደንበኛው ያሳውቃል።ተጠርጣሪው ወይም ተከሳሹ ወይም ታራሚው በማቆያ፤በማረፊያ ወይም በማረሚያ ቤት በሚገኝበት ጊዜ ከጥብቅና አገልግሎት ጋር ተያያዥነት ያላቸውን መረጃዎች ይቀበላል፤ይሰጣል።

2. የፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን በተመለከተ ስናይ የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን ዋና እና ምትክ ስልጣን ሲሆን በኢትዮጵያ ግዛት ክልል በሚፈጸም ወንጀል ላይ ቀዳሚ የዳኝነት ሥልጣን አላቸው፤በኢትዮጵያ መርከብ ወይም አይሮፕላን ላይ ከኢትዮጵያ ግዛት ውጪ የተፈጸመ ወንጀል በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ እንደ ተፈጸመ

---

[52]የይቅርታ አሰጣጥ እና አፈጻጸም ስርዓት አዋጅ፤2006፤ነጋሪት ጋዜጣ፤አዋጅ ቁጥር 840.

[53]የፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ዓቃቢ ሕግ ማቋቋሚያ አዋጅ፤2008፤ነጋሪት ጋዜጣ፤አዋጅ ቁጥር 943፤22ኛ አመት፤ቁጥር 62።

[54]የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌደራል ፍ/ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ፤የካቲት 1988፤ነጋሪት ጋዜጣ፤አዋጅ ቁጥር 25፤2ኛ አመት ቁጥር 13(ከዚህ በኋላ በዚህ ጽሁፍ የፌደራል ፍ/ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ የምንለዉ)(ማሻሻያወች 138/91፤254/1993፤321/1995፤454/2005 ያካትታል)።

ይቆጠራል፤ወደ ጎረቤት አገሮች በሚደረግ የየብስ ጉዞ በመጓጓዣ ላይ በተፈጸመ ወንጀል፤በኢትዮጵያ መንግሥት በደህንነቱ ወይም በአንድነቱ ላይ፣በሕጋዊ ተቋማቱ ወይም በዋና ዋና ጥቅሞቹ ወይም በገንዘቡ ላይ በሚፈጸም ወንጀል፣በሀገር፣በሕዝብ ሞራልና ደህንነት ላይ በሚፈጸም የኮምፒዩተር ወንጀል ላይ የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ቀዳሚ የዳኝነት ሥልጣን አላቸው እንዲሁም ወንጀል በተፈጸመበት አገር ሕግ መሠረት ዳኝነት ካላገኘ የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን አላቸው።በውጭ ሀገር ፍርድ ቤቶች የተሰጡ የወንጀል ፍርዶችን የማስፈፀም ስልጣን አላቸዉ።[56]

3. የፌዴራል ፍርድ ቤቶች በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ የወል የዳኝነት ሥልጣን አላቸው። አፈጻጸማቸው የፌዴራል መንግሥት ወይም በአንድ የክልል መስተዳድር በሚያስተዳድረው የአስተዳደር ክልል ወሰን ያልተገደቡ ወንጀሎች፤ዓለም አቀፍ ባሕርይ ያላቸው ወይም ድንበር ተሻጋሪ ወንጀሎች፤ከውጭ ጉዳይ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ወንጀሎች፤ወታደራዊ ወንጀሎች፤በፌዴራል መንግሥቱ ተቋማት፣ንብረት፣ሰነድ እና ገንዘብ ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች፤በፌዴራል መንግሥቱ ባለሥልጣናት እና ሠራተኞች ከኃላፊነት ጋር በተያያዘ የሚፈጸም ወንጀል፤ለፌዴራል መንግሥቱ ተጠሪ በሆኑ ከተሞች ወይም ቦታዎች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች፤የጉምሩክና የፌዴራል መንግሥት ግብርና ገንዘብ ነክ ጥቅሞች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች፤በፌዴራል ሥርዓቱ ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች የፌደራል ፍ/ቤቶች የወል የዳኝነት ሥልጣን አላቸው በሌላ በኩል የክልል ፍርድ ቤቶች በአፈጻጸማቸው የክልል መንግሥት ላይ የሆኑ ወይም ከአንድ የአስተዳደር ክልል በላይ ባልሆኑ ወንጀሎች፤አንድ ክልል ከሚያስተዳድረው የአስተዳደር ክልል በላይ በሆኑ ቀላል የወንጀል ጉዳዮች፤እና ለፌዴራል ፍርድ ቤቶች ባልተሰጡ ጉዳዮች ላይ የወል የዳኝነት ሥልጣን አላቸው፤ከላይ የተደነገገው ቢኖርም የኦሮሚያ ፍርድ ቤቶች በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባለው የክልሉ መንግሥት ተቋማት፣ንብረቶች፣ገንዘብ እና ሰነዶች ላይ በሚፈጸሙ ወንጀሎች ላይ የወንጀል የዳኝነት ሥልጣን አላቸው።ከላይ የተገለጹት የዳኝነት ስልጣን የዚህ ሕግ አካል በሆነው ሰንጠረዥ"ሀ"ተደልድሏል፤[57]በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ የተደነገገው ቢኖርም ክልሎች የክልላቸውን ነባራዊ ሁኔታ መሠረት በማድረግ የዳኝነት ሥልጣንን በሚያወጡት ሠንጠረዥ ሊወስኑ ይችላሉ። በዚህ ረቂቅ የወ/ሕ/ሥ/ሥ እና የማስረጃ ሕግ በፌደራል ፍ/ቤቶች መደበኛ፣ይግባኝ እና ሰበር ስልጣኑን በተመለከተ የፌደራል ፍ/ቤቶች ጠቅላይ ፍ/ቤት፣ከፍተኛ ፍ/ቤት እና መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሚያዋቸዉ ጉዳዮች በፌደራል ፍ/ቤቶች ማቆቋሚያ አዋጅ ቁጥር 25/88 እና ማሻሻያወችን ባሻሻለ መልኩ እንዲሁም ከአንድ እስከ አምስት ዳኞች የሚይዙትን ጉዳይ በዝርዝር ለማስቀመጥ ተሞክሯል። እንዲሁም መደበኛ፣ይግባኝ እና ሰበር ስልጣኑን በተመለከተ የክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት፣ከፍተኛ ፍ/ቤት እና ወረዳ ፍ/ቤት ስልጣን የሚያዩዋቸዉ ጉዳይ መሰረት ተደርጎ ባሻሻለ በዝርዝር ለማስቀመጥ ተሞክሯል። ሌላዉ የአስተዳደር ወሰን የዳኝነት ሥልጣን እና የፍትህ ተቋማት የፌደራል ተቋማት በራሳቸዉ የሚሰሩበት እና ካልቻሉ ከወጭ እና ከባለሙያ እጥረት አንጻር በቀድሞዉ መግባቢያ ሰነድ የምንለዉ አሁን በረቂቁ ህግ በግልጽ ለክልል ዉክልና እንዴት መስጠት እንዳለበት ተዘርዝሮ እናገኘዋለን፤የፍትህ አካላት ከምርመራ፣ከክስ እና ከማከራከር በራሳቸዉም ሆነ በአቤቱታ ጉዳይን ከማየት የሚገለሉበትን፤ክስ ማዛወር በተመለከተ በረቂቁ ስነስርዓቱ ተዘርዝሮ እናገኘዋለን።

[56] ዝኒ ከማሁ።

[57] ረ/የወ/ሕ/ሥሥ/ እና ማ/ሕ/።

4. የንብረት እግድ እና አስተዳደር መርህ በዚህ ረቂቅ የተካተተ ሲሆን ተፈጽሟል ከተባለው ወንጀል ጋር ግንኙነት ያለው ማንኛውም ንብረት ወይም ገንዘብ በፍርድ ቤት ትእዛዝ መሠረት ሊታገድ፣ሊያዝ እና አግባብነት ባለው አካል ሊተዳደር ይችላል፡፡በዚህ ሕግ በተለየ ሁኔታ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በፍርድ ቤት፡-(ሀ)በወንጀል ሕግ ሊወረስ የሚችልን ንብረት ሲሆን፣(ለ)በግለሰብ እጅ እንዳይገባ የተደነገገ ወይም ልዩ ፍቃድ የሚያስፈልገው ንብረት ሲሆን በዚህ ሕግ መሠረት ሊታገድ ይችላል፡፡ነገር ግን ለተከሳሹ እና ለቤተሰቡ የእለት አገልግሎት የሚጠቅሙ የቤት ውስጥ መገልገያ እና ተከሳሽ ቤተሰቡ የሚተዳደሩበት ሌላ ንብረት የሌላቸው ሲሆንና፣የሚተዳደሩት ከታገደው ንብረት ከሚገኝ ገቢ ከሆነ መሰረታዊ ፍላጎትን ለማሟላት ለተከሳሹና ለቤተሰቡ ፍርድ ቤቱ በቂ ነው ብሎ የሚገምተውን ያህል ገቢ አይታገድም፡፡ሌላዉ በረቂቅ ህጉ የንብረት እግድ ማመልከቻ እንዴት ይቀርባል?፣እንዴት የእግድ ትዕዛዝ ይሰጣል?፣እንዴት ይሻሻላል ወይም ይነሳል?እንዲሁም እግዱ እንዴት ቀሪ ይሆናል?የሚሉት ነጥቦች ተዘርዝረዉ እናገኘዋለን፡፡[58]

ክፍል 4

በረቂቁ ወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ እና በማ/ሕግ የተካተቱት አዲስ ጽንሰ ሃሳቦች

1. የወንጀል ጉዳይ ውሳኔ የሚሰጥባቸው አማራጭ መንገዶችና መፍትሔዎች በዚህ ረቂቅ ሕግ መካተቱ ይበል የሚያስብል ነዉ በግል ተበዳይ የሚቀርብ እርቅ[59] በስራ ላይ ባለዉ የወ/ሕ/ሥ/ሥ ከመገለጹ ዉጭ በወንጀል ህግ አዲስ ጽንሰ ሃሳብ ነዉ፡፡ይህን በተመለከተ የህግ ምሁራን ብዙ ዓላማ እና ጥቅም ስላለዉ በትምህርት፣በስልጠና እና በምርመራቸዉ ሲገልጹት ቆይተዋል፡፡[60]አማራጭ መንገዶች ዓላማ በወንጀል ፍትሕ ሥርዐት የማኅበረሰቡን ተሳትፎ በማረጋገጥ፣እውነትን በማውጣት፣የወንጀል ጉዳዮችን ሰላማዊ፣ቀልጣፋና ወጭ ቆጣቢ በሆነ መልኩ ዘለቄታዊ ዕልባት እንዲያገኙ ማስቻል ነው፡፡የአማራጭ መንገዶች እርቅ፣የጥፋተኝነት ድርድር የባሕላዊ ተቋማት ሥርዐት ሲሆኑ ዝርዝር አላማቸዉ ስንመለከት፦

1.1. የእርቅ ዓላማ ተደጋጋሚ ወንጀሎችን እና ተደራራቢ ክሶችን በመቀነስ በግል ተበዳይ እና በተከሳሽ ወይም በቤተሰቦቻቸውና በሚገኙበት ማኅበረሰብ መካከል የተፈጠረውን አለመግባባት በማስቀረት ሰላምን ማረጋገጥ ነው፡፡[61]

1.2. የጥፋተኝነት ድርድር ዓላማ ተከሳሹ ለተፈፀመው የወንጀል ድርጊት በራሱ ነፃ ፍቃድ የእምነት ቃል እንዲሰጥ፣ እንዲፀፀት እና እንዲታረም እድል መስጠትነው፡፡[62]

1.3. በባሕላዊ ሥርዐት እንዲታይ የሚቀርብ ጥያቄ አቀራረብ ዐቃቤ ሕግ በራሱ አነሳሽነት ወይም በግል ተበዳይ ወይም በባሕላዊ ሥርዐት ሥልጣን ባለውሰው፣አግባብ በሆነ የመንግስት አካል፣ጉዳዩን በሚያየው ፍርድ ቤት ጠያቂነት ተጠርጣሪው ወይም ተከሳሹ

---

[58]ንብረቱ ሊወረስ የሚችለዉ በወ/ህ/ቁ.98፣100 እና 140 በህጉ ተደንግጎ ሲገኝ እና ንብረቱ የወንጀል ፍሬ ሲሆን መሆኑን ተወስኖ እናገኘዋለን (በፌ/ጠ/ፍ/ቤ/ሰ/ሰ/ች ቅጽ 14 መ/ቁ.75387)፡፡

[59]ይቅርታ በወንጀል ህግ ቁጥር 230 የተደነገገ ሲሆን በወንጀለኛዉ መዝገብ ላይ ተመዝግቦ የሚገኝ ሲሆን የጥፋተኛነት ዉሳኔ እንዳልነበረ የሚያስቀር አይደለም ስለሆነም ድጋሜ ወንጀል ፈጽሞ ተከሶ ጥፋተኛ ከተባለ በይቅርታ የወጣበት ወንጀል በሪከርድነት ሊያዝ የሚገባ መሆኑን ተወስኖ እናገኘዋለን (ፌ/ጠ/ፍ/ቤ/ሰ/ሰ/ች ቅጽ 10 መ/ቁ. 41248)፡፡

[60]አማራጭ የሙግት መፍቻ መንገዶች (Alternative dispute resolution) ጥቅሙ ከረቂቅ ህጉ አንጻር ከመግለጽ ዉጭ ዝርዝር አላማ እና ጥቅም በሁለተኛ ዲግሪ የጻፍኩት ተርም ፔፐር ስላለ በሌላ ጽሁፍ እንገናኛለን ብየ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡

[61] ረ/የወ/ሕ/ሥሥ/ እና ማ/ሕ/ አንቀጽ 164-168

[62] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 169-179፡፡

ፈጸመ የተባለው የወንጀል ድርጊት በባሕላዊ መንገድ እንዲታይ ሊፈቅድ ይችላል፡፡ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ የሚዘረጋውን ሌሎች የመፍትሔ ርምጃ ሥርዐት ተግባራዊ የሚደረግ መሆኑን በተጨማሪነት ተደንግጎ እናገኘዋለን፡፡ከላይ የተገለጹት አማራጭ መንገዶችና መፍትሔዎች በተመለከተ ሥነሥዓቱን እና አፈጻጸሙን በተመለከተ በዝርዝር ተደንግጎ እናገኘዋለን፡፡[63]

2. የመጨረሻ ፍርድን እንደገና የማየት ሂደት ዓላማ በተባባ ፍርድ ንፁሃን እንዳይቀጡ ፍርዱን ለማረም ነው፡፡በሌላ በኩል ሕግ ባለሙያወች ሊያነሱት የሚችሉት ስጋት ከዚህ አላማ ዉጭ አሳማኝ ማስረጃ ሳይኖር ፍርድ እንደገና ይታይ በማለት የፍ/ቤትን መዝገብ መጨናነቅ ስራ ጫና ሊኖር ይችላል የሚል ሲሆን በቂ ባለሙያ በመመደብ ይህን ስጋት መቀነስ ይቻላል ሌላዉ ንጹህ ሰዉ መጀመሪያ አላግባብ እንዳይፈረድበት መጠንቀቅ አለብን ይህም ከታለፈ ፍርድ እንደገና ሲታይ ተገቢዉን ጥንቃቄ ማድረግ ይጠበቅብናል፡፡የወንጀል ፍርድ እንደገና እንዲታይ በቂ ማስረጃ ሲኖር ይኸዉም ፍርድ ከተሰጠ በኋላ ጥፋተኛውን ነፃ ሊያደርግ የሚችል ጠቃሚ ማስረጃ ከተገኘ፣ከፍርድ በኋላ በሳይንሳዊ ዘዴ የተገኘ እውነት እንደሆነ፣ ከጉዳዩ ጋር በተያያዘ ዳኛው ኃላፊነቱን አጓድሏል ተብሎ በወንጀል ጥፋተኛ ከተባለ፣በጉዳዩ ላይ ሌላ በነፃ የተለቀቀ ሰው ከፍርድ ቤት ውጭ በሚታመን ሁኔታ ወንጀሉን መፈጸሙ ጥፋተኛነቱን በማመን ቃል የሰጠ እንደሆነ፣ወይም እውነተኛ መስሎ የቀረበ ማስረጃ በሐሰት ወይም በማጭበርበር መዘጋጀቱ ሲረጋገጥ ነው፡፡[64]

3. በወንጀል ጉዳይ የሚደረግ የዓለም አቀፍ ትብብር ዓላማ ሀገሪቱ በወንጀል ጉዳይ ከሚደረግ ትብብር ጋር በተያያዘ በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚኖሩ መብትና ጥቅሞችን ለማስከበር እና ግዴታዎችን በአግባቡ ለመወጣት የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋት ነው፡፡ትብብር ማድረግ የማይፈቀድባቸው ሁኔታዎች ከመንግስት ጋር በወንጀል ጉዳይ ላይ የሚደረግ የትብብር ጥያቄ፡የማንኛውንም ሰው መሠረታዊ መብቶችና ነፃነቶች ሊጥስ ይችላል ተብሎ የሚታመን እንደሆነ በተለይም ለግርፋት፣ጭካኔ፣ኢ-ሰብዓዊ ለሆነ አያያዝ ወይም ቅጣት ይጋለጣል ተብሎ ሲታመን፤ወይም አንድን ሰው በዘር፣በብሔር ማንነት፣በኃይማኖት፣በፆታ፣በቀለም በዜግነት ወይም ባለው የፖለቲካ አቋም ሊያስከስሰው ወይም ሊያስቀጣው ይችላል ተብሎ ሲታመን፤ለተጠየቀው ትብብር መነሻ የሆነውን በጦር ሕግ ብቻ የሚያስቀጣ ተግባር ጋር የተያያዘ የትብብር ጥያቄ ሆኖ ለወንጀሉ የተቀመጠውን ቅጣት የመወሰን ሥልጣን የተሰጠው ለልዩ ፍርድ ቤት ወይም የአስተዳደር ፍርድ ቤት እንደሆነ፤የትብብር ጥያቄው አንድ ሰው ተከሶ ነፃ ከተባለበት፣ቅጣት ከተጣለበት፣ይቅርታ በተደረገበት ወይም ቅጣቱን ከፈጸመበት የወንጀል ድርጊት ጋር የተያያዘ ከሆነ፤የቀረበው የትብብር ጥያቄ የሀገርን ሉዓላዊነት፣የሀገርና የሕዝብ ደህንነትን፣የሕግ የበላይነት ወይም የሀገር ጥቅምን የሚነካ ከሆነ፤ትብብር መደረግ የለበትም፡፡ለትብብር የሚላከው ሰው ኢትዮጵያዊ እንደሆነ በሕገ መንግሥቱ የተመለከቱ መብቶችና ነፃነቶች እንደሚከበሩለት መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ የትብብር ጥያቄ የቀረበበት ጉዳይ የክስ ማቅረቢያ ወይም የቅጣት ውሳኔ ማስፈጸሚያ የይርጋ ጊዜ በወንጀል ሕግ መሠረት ይቆጠራል፡፡የትብብር አይነቶች በወንጀል ጉዳይ የሚደረግ ትብብር በወንጀል ምርመራ፣ክስ እና የፍርድ ሂደት ባሉ ጉዳዮች ያጠቃልላል፡፡

አሳልፎ ለመስጠት በቀረበ ጥያቄ ላይ የሚፈጸም ሥነ-ሥርዐት በስምምነት በሌላ ሁኔታላልተገለጸ በስተቀር፣ሁለት ዓመትና በላይ በእሥራት ወይም በሞት ሊያስቀጣ የሚችል የወንጀል ተግባር ለወንጀል የክስ ሂደት ወይም ቅጣትን ለመወሰን፣ ወይም ስድስት ወር እና በላይ ያልተፈጸመ ወይም ሳይፈጸም የቀረ የእሥራት ቅጣትን ለማስፈጸም፣አሳልፎ የመስጠት

[63] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 189-196፡፡
[64] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 365-389፡፡

ጥያቄ ሊቀርብበት ይችላል፡፡ከዚህ በላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ተላልፎ እንዲሰጥ የተወሰነበት ሰው የተከሰሰበት ወይም ጥፋተኛ የተባለበት ሌላ ተደራቢ ወንጀል ከሁለት ዓመት በታች በእሥራት ሊያስቀጣ የሚችል ወይም ፍርደኛው ሳይፈጽመው የቀረ ከስድስት ወር በታች የእሥራት ቅጣት እንደሆነ ተላልፎ ሊያሰጥ ይችላል፡፡ በጣምራ የወንጀል ድርጊት ጊዜ ድርጊቱ ወይም በድርጊቱ ምክንያት ተወስኖ ሳይፈጸም የቀረ ቅጣት በውጭ ሀገር እና በኢትዮጵያ ሕግ ወንጀል ወይም ቅጣት የሚያስከትል መሆኑ የተደነገገ ካልሆነ በቀር ተላልፎ አይሰጥም፡፡ የትብብር ጥያቄ የሚመለከተው ወንጀል ወይም ቅጣት በውጭ ሀገርና በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት በአንድ ዓይነት ስያሜ አለመጠራቱ ወይም በተመሳሳይ የወንጀል ድንጋጌ ሥር አለመጠቀሱ ወይም በአንድ ዓይነት አገላለጽ አለመቀመጡ አሳልፎ የሚያሰጥ ወንጀል ወይም ቅጣት መሆኑን አያስቀረውም፡፡

አሳልፎ መስጠት የማይፈቀድባቸው ሁኔታዎች ተላልፎ ይሰጠኝ ጥያቄ የቀረበበት ሰው፡-የኢትዮጵያ ዜግነት ያለው ከሆነ፣በተከሰሰበት ወይም ጥፋተኛ በተባለበት አሳልፎ በሚያሰጥ የወንጀል ተግባር አስቀድሞ በኢትዮጵያ ወይም በሌላ ሀገር ፍርድ ቤት በተሰጠ የመጨረሻ ውሳኔ ቅጣት ተወስኖበት የፈጸመ፣ወይም በኢ/ፌ/ዴ/ሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 28(1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በኢትዮጵያ ወይም በጠያቂው ሀገር ሕግ መሠረት ጥያቄው በቀረበበት ወቅት በይቅርታ፣በምህረት፣በይርጋ የታገደ ወይም ከመከሰስ ወይም ከቅጣት ነፃ የሚያደርግ ማንኛውም ምክንያት ያለ እንደሆነ ተላልፎ አይሰጥም፡፡የወንጀል ክስ ወጪዎች በጠቅላላው የዐቃቤ ሕግ የክስ ወጪ፣በግል አቤቱታ የሚቀርብ የወንጀል ክስ ወጪ፣ የፍትሐብሔር ክርክር ወጪና ኪሳራ፣የምስክር ወጪ ማን መሸፈን እንዳለበት በዝርዝር ተደንጎ እናገኘዋለን፡፡[65]

በመጨረሻም ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን ለፍትህ አካላት የተሰጠዉን ስልጣን ተዘርዝሮ እናገኘዋለን፡፡ይህንን ሕግ ለማሻሻል የሚቀርብ ማንኛውም የማሻሻያ ሀሳብ በፍትሕ አካላት ውይይት ተደርጎበት በፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ በኩል በሚኒስትሮች ምክር ቤት ሲፀድቅ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መቅረብ ይኖርበታል፡፡[66]

[65] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 438-441፡፡
[66] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 442-443፡፡

ዋቢ ሕጎች እና ዉሳኔወች

1. የሲቪል እና የፖለቲካ መብቶች አለም አቀፎች ቃልኪዳን፣በጠቅላላ ጉባኤዉ የተዘጋጀዉ በ2200A (XXI)።
2. የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት፣1987፣ነጋሪት ጋዜጣ፣አዋጅ ቁጥር 1፣1ኛ ዓመት፣ቁጥር 1።
3. የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ሕግ ሥነ-ሥርዓት እና የማስረጃ ሕግ፣ረቂቅ።
4. የኢትጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲ ሪፐብሊክ የወንጀል ሕግ አዋጅ፣1996፣ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ፣አዋጅ ቁጥር 414።
5. የኢትጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ፍትህ ፖሊሲ፣የሚኒስተሮች ምክር ቤት፣የካቲት 25፣2003።
6. የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ ማቋቋሚያ አዋጅ፣2008፣ነጋሪት ጋዜጣ፣አዋጅ ቁጥር 943፣22ኛ አመት፣ቁጥር 62።
7. የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌደራል ፍ/ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ፣የካቲት 1988፣ነጋሪት ጋዜጣ፣አዋጅ ቁጥር 25፣2ኛ አመት ቁጥር 13።
8. የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት አዋጅ፣1954፣ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ፣አዋጅ ቁጥር 1።
9. የይቅርታ አሰጣጥ እና አፈጻጸም ስርዓት አዋጅ፣2006፣ነጋሪት.ጋዜጣ፣አዋጅ ቁጥር 840።.
10. የፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን መተዳደርያ ደንብ፣2005፣ነጋሪት ጋዜጣ ፣ደንብ ቁጥር 268።
11. የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ዉሳኔዎች፣ቅጽ 1-23፣የኢፌዲሪ ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣አዲስ አበባ።